# ትምህርተ ሃይማኖት




የደብረ ከዋክብት
አቡነ አረጋዊና ቅዱስ ገብረክርስቶስ
ቤተክርስቲያን
የፈለገ ሰላም ሰንበት ት/ቤት

አዳጊ ሣልሳይ
፳፻፲፮ ዓ.ም

ምዕራፍ - ፪

## ምዕራፍ ፪ (ሁለት)

## ነገረ እግዚአብሔር

### ⌖ ህልዎተ ፈጣሪ/እግዚአብሔር

- ህለወ ማለት ኖረ ማለት ሲሆን ህልዎተ ፈጣሪ ማለት የፈጣሪ መኖር ማለት ነው፡፡
- አንድም እግዚአብሔር ያልኖረበት ዘመን ሳይኖር የእግዚአብሔር መኖር ማለት ነው፡፡ ሰው ያልነበረበት ሰከንድ፣ ደቂቃ፣ ሰዓት፣ ቀን… ዘመን አለ፤ ስለሰው መኖር ስናወራ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከዚህ እንላለን፤ መነሻ እና መድረሻ፣ መጀመሪያ መጨረሻ ስላለው፤ እግዚአብሔር ግን ያልኖረበት ጊዜ የለም፤ ጥንት ከሌለው ጥንትነቱ ጀምሮ መጨረሻ እስከሌለው መጨረሻነቱ ድረስ የማይኖርበት ጊዜ የለም ይህን የምርዳበት ትምህርት ማለት ነው፡፡
- አንድም ህልዎተ እግዚአብሔር ማለት እግዚአብሔር አብ በእግዚአብሔር ወልድ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፤ እግዚአብሔር ወልድ በእግዚአብሔር አብ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፤ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ወልድ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በሕልውና መኖር(ሕልው መሆን) ማለት ነው፡፡

"እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፤" ዮሐ ፲፬፥፲፩

"ነአምን ከመ አብ በወልድ ወበመንፈስ ቅዱስ ወወልድ በአብ ወበመንፈስ ቅዱስ ወመንፈስ ቅዱስ በአብ ወበወልድ ዛቲ ሥላሴ ዕሪት እንበለ ፍልጠት ወዘእንበለ ውላጤ በሠለስቱ አካላት ወአሐዱ መለኮት - አብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ሕልው እንደሆነ፤ ወልድም በአብ በመንፈስ ቅዱስ ሕልው እንደሆነ መንፈስ ቅዱስም በአብ በወልድ ሕልው እንደሆነ እናምናለን፡፡ ይህቺ ሦስትነት ያለመለየት ያለመለወጥ በሦስት አካላት በአንድ መለኮት የተካከለች ናት" (ሃይ.አበ ፲፩፡5) ሕልው ማለት አንዱ አካል በአንዱ አካል የሚኖር ነው ማለት ነው፡፡

- ዓለማችን እንደ ፈረስ ጆሮ እንደ ጦር ጉሮሮ ተካክላ እግዚአብሔር የለም በሚል ሰው ሰራሽ አስተሳሰብ፣ በገንዘብ ድቃቂ፣ በጨርቅ እላቂ ተታላ፣ እንዲሁም ዕውቀት ከማጣት የተነሳ፣ሳታውቅ ያወቀች መስሏት የፈጠራትን ረስታ፣ በከንቱ ርዕዮት መውደቋ ይታወቃል፡፡

"ስለዚህ ትዕቢት ያዘቸው፤ ኃጢአትንና በደልን ተጐናጸፉአት። ዓይናቸው ስብ ስለ ሆነ ወጣ፤ ልባቸውም ከምኞታቸው ይልቅ አገኘ። አስበው ክፉ ነገርን ተናገሩ፤ ከፍ ከፍ ብለውም በዓመፃ ተናገሩ። አፋቸውን በሰማይ አኖሩ፥ አንደበታቸውም በምድር ውስጥ ተመላለሰ። ስለዚህ ሕዝቤ ወደዚህ ይመለሳሉ፤ ፍጹም ጊዜም በላያቸው ይገኛል፤ እግዚአብሔር እንዴት ያውቃል? በልዑልስ ዘንድ በውኑ እውቀት አለ? ይላሉ።" መዝ 72/73፡6፡10

- በሰማይ ቅድምናውን በምድር ድኅርናውን ካዱ በማለት ቅዱስ ዳዊት በትንቢት መነጽርነት በቅድምናው የተነሡ ከሃድያንንና በድኅርናው የተነሱ ዕልዋን(እግዚአብሔር የለም ባዮችን) ገስጿቸዋል፡፡

### 🕮 በእግዚአብሔር መኖር የፈላስፎች አስተሳሰብ እና እውነተኛ ፍልስፍናና እውነተኛ ፈላስፎች

- ፍልስፍና ማለት ጥበብ፣ ብልሃት፣ ዕውቀት፣ ፍቅረ ጥበብ(ጥበብን መውደድ) ማለት ነው፡፡
- ዓለም ከዕለት ወደ ዕለት ከጥንት ጀምሮ እውነተኛ እና ሐሰተኛ ፈላስፎች የሚወጡባት ናት፡፡ በዘመናችን ግን ከእውነተኛው ይልቅ ሐሰተኛው እየበዛባት ትገኛለች፡፡
- እውነተኛ ፈላስፋ መሆን ያለበትን፣ እንደሆነ ማየት የቻሉ ናቸው፡፡ ማለትም ተፈጥሮን በተፈጥሮነቱ ማየት የቻሉ ሲሆኑ፣ በዚያውም ላይ ሰው የመሆንን አስተሳሰብና ሰውን የፈጠረው እንደሸት ፈልፍሎ እንደ ዘንግ መልምሎ እጅግ መልካም አድርጎ የሠራው እግዚአብሔር መሆኑን የሚያምኑ ናቸው፡፡

"እውነተኛ ፍልስፍና ክርስትና(ከኢአማንያን መለየት) ትልቁ ፍልስፍና ምንና(ከተድላ ዓለም መለየት) ነው" ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳለ

- በእውነተኛ ፍልስፍና ላይ የተቀመጡ ሰዎች እውነት የሆነውን ለማግኘት ይጥራሉ፤ እውነት አንድ ብቻ ስለሆነም ጭምር በእውነትነቱ ያገኙታል፡፡
- እውነተኛ ፍልስፍና በእውነተኞች ሰዎች ግብር የተገለጠ የእውነትን እውነትነቷን የገለጠ በእውነት የኖረ ነው፡፡ እንደ ማሳያ ያህል ቅዱሳን ሊቃውንት የግሪክ እና የአቴና ፍልስፍና ሳይገድባቸው በመመነን ዓለምን ወደ ጣዕመ ሃይማኖት ያመጡበት መስመር ነው፡፡
- ለዚህም ዋና ዋና ተጠቃሾች እንደ አባ አርሳንዮስ(በፍልስፍናው ታዋቂ እንደመሆኑ እስከ ቤተመንግሥት ድረስ ስመ ጥር ነበር)፣ ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ፣ ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ()፣ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ዘቆጵሮስ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፣ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፣ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፣ ቅዱስ ቶዎዶጦስ ዘእንቆራ፣ ቅዱስ ኤራቅሊስ፣ ቅዱስ ሱንትዩ ያሉት ናቸው፡፡
- እነዚህ ሁሉ ከላይ የጠቀስናቸው በነበሩበት ዘመን አንቱ የተባሉ ታላላቅ ፈላስፎች ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ፍልስፍናቸው ከፍልስፍና ባለቤት፣ ከፈላስፎች አምላክ ከእግዚአብሔር የሚያርቅ አልነበረም፡፡ ከዚህ የተነሳ የሥጋዊ ፍልስፍና ተራነቱን እንዲረዱት እና በመንፈሳዊው ፍልስፍና አሸተው ("ተ" አይጠብቅም) መጠቀሚያ እንዲያደርጉት አስችሏቸዋል፡፡
- ክርስትና ጸረ ፍልስፍና ወይም ህየንተ ፍልስፍና ሳይሆን መልዕልተ ፍልስፍና ነው፡፡ አመክንዮን አይነቅፍም፣ አመክንዮን ብቻም አይጠቀምም፡፡ ከአመክንዮ በላይ የሆኑ ጉዳዮችን አሜን ብለን እንድንቀበል ያደርገናል እንጂ፤

- ስለዚህ ክርስትና ከፍልስፍና ሁሉ በላይ ነው:: ክርስትና ያልመዘነው ፍልስፍና የለም፤ በፍልስፍና ግን ሊመዘን አይችልም! ቅዱሳት መጻሕፍት ያልመዘኑት ሳይንስ የለም:: ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚመዝን ሳይንስ ግን የለም:: እውነት ከሁሉ በላይ ናትና ሌሎች ሁሉ ከእርሷ በታች ናቸው::

**በሥጋዊ ፍልስፍና እና በመንፈሳዊ ፍልስፍና መካከል ያለው ልዩነት**

- ሥጋዊ ፍልስፍና ከዕለት ወደ ዕለት እጼት ኑሮውን ማሳለጥና እንጼት የዕለት ጉርስን ማግኘት እዳለበት ያመለክተዋል:: መንፈሳዊ ፍልስፍና ግን እንጼት መጾም፣ ምግብ ባለመብላት ረሃብን እንዴት ማሸነፍ እንዳለበት ያመለክተዋል::
- ሥጋዊ ፍልስፍና አሸንፎ ከሁሉ በላይ እንዲሆን ያነሳሰዋል፤ መንፈሳዊ ፍልስፍና ደግሞ ከሁሉ በታች መሆን ትህትና እንጂ ሽንፈት እንዳልሆነ ያስገነዝበዋል::
- ሥጋዊ ፍልስፍና አንዱን በመጉዳት የበላይነት ማወጅ፣ ቀምቶ ወይም አሸንፎ መኖር የዓለም ፍልስና ዘይቤ  ነው:: መንፈሳዊ ፍልስፍና ግን ስለ ሰው መኖርን ለሌላው መራራትን ያስገነዝባል::
- ሥጋዊ ፍልስፍና ሃሳብን በሃሳብ ማሸነፍ ነው እንጂ ሃሳብን በእውነት ማሸነፍ አይደለም!

**ምሳሌ፡-** አንድ ፈላስፋ አንድ ዓመት ወደ አስተማራቸው ተማሪዎች ሄዶ ፈተናውን በፍጥነት መልሱ ብሎ ፈተና ሰጣቸው:: አንድ ወንበር አንሥቶ ከጠረጴዛው ላይ  አኖረውና ሁላችሁም ዚህን ወንበር አለመኖር ጽፋችሁ ስጡኝ አላቸው:: ሁሉም የሚጽፉትን ሲፈላሰፉ አንዱ ግን በፍጥነት ጽፎ ሰጠው:: ኋላም መልሳችሁን አቅርቡ አለ:: ፈጥኖ ከሰጠው ካንዱ በቀር መልሱን ያገኘው የለም መልሱም እንዲህ ይል ነበር "የቱ ወንበር?"

አሁን በግዘፍ የሚያየውን ወንበር አለ ለማለት ተቸግሮ የለም ለማለት ከተገደደ፣ በረቂቅነት በምልዓት ያለ እግዚአብሔርን የለም ቢል ምን ያስደንቃል? ኅጸተ አእምሮ(የአእምሮ ጉድለት) እና እብደት ነው ብሎ ማለፍ ነው እንጂ::

## <u>ከአምላክ መኖር ጋር በተያያዘ የተለያዩ አሳቤዎች የሚሰጡ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ዋነኞቹን እንመለከታለን፡-</u>

- **ቲዝም** (Theism) ፡- ይህ በአምላክ መኖር የሚታመን እሳቤ ነው:: በዚህ እሳቤ ውስጥ የተለያዩ አስተሳሰቦች አሉ!
  - **ሞኖቲዝም** (Monotheism) ፡- የአንድ አምላክ መኖር እምነት ነው:: **አማኞቹ ሞኖቲስት** (Monotheist) ይባላሉ:: ለምሳሌ ፡- ክርስቲያኖች፣ አይሁዳውያን እና ሙስሊሞች፤
  - **ፖሊቲዝም** (Polytheism) ፡- የብዙ አማልክት መኖር እምነት ነው:: አማኞቹ **ፖሊቲስት** (Polytheist) **ይባላሉ::**
  - **ዲዝም** (Deism) ፡- ፈጥሮ ዞር ያለ አምላክ መኖር እምነት ነው:: አማኞቹ **ዲስት** (Deist) ይባላሉ፤ በአምላክ መኖር ያምኑና ግን ደግሞ ያ አምላክ ፍጥረትን ፈጠረና ከዚያም ራሱን ከፍጥረቱ ለየ ወይማ አራቀ፤ አሁን ፍጥረትን እያስቀጠለ ያለው እርሱ አይደለም!
    - **ምሳሌ፡-** አንድ ሰዓት ሠሪ አንዴ ሰዓቱን ካበጀው በኋላ ሰዓቱ በራሱ እንደሚሽከረከር እንዲሁ ፈጣሪም አንዴ ዓለምን ካበጃጀ በኋላ ዓለም በራሷ ትቀጥላለች አምላክ አያስፈልጋትም የሚሉ ናቸው::
- **ኤቲዝም** (Atheism) ፡-  ይህ እሳቤ አምላክ የለም የሚል ነው:: ተከታዮቹም ኤቲስት ይባላሉ፤ ሁለት ዓይነት ኤቲዝም አለ ፡-
  - አምላክ በፍጹም የለም የሚል - Strong Atheism
  - ለአምላክ መኖር በቂ ማስረጃ ማቅረብ አይቻልም የሚል - Weak Atheism
  - ኤቲስቶች አምላክ ላለመኖሩ ምንም ዓይነት ማስረጃ አያቀርቡም ብሎ ለመናገር ያስደፍራል:: አምላክ አለመኖሩን የሚያሳዩት "አምላክ ለመኖሩ ምንም ማስረጃ የለም" በሚል እንጂ እነርሱ ራሳቸው አምላክ አለመኖሩን ተመራምረው ደርሰውበት አይደለም::
  - አምላክ ለመኖሩ ማስረጃ ባይኖር ራሱ ማስረጃ ስላልቀረበ በቃ አምላክ የለም ማለት ነው ብሎ መደምደም "Argument from ignorance" የተሰኘ ተፋልሶ "Fallacy" ነው::
  - ከቀድሞው ዘመን ጀምሮ ለአምላክ አለመኖር ማስረጃ ተብሎ የሚሰጠው ዓለም ላይ የሚታዩ ክፋቶች ናቸው:: ዓለም ላይ ክፋቶችን የምናየው አምላክ ስለሌለ ነው፤ አምላክ ቢኖር ክፋቶችን ያስቀም ነበር:: ለምሳሌ፡- ረሃብ፣ ግድያ፣ መደፈር... ወዘተ
  - እውን ክፋቶችን ማየታችን ግን አምላክ እንደሌለ ያሳያል? ለኤትስቶችስ ማስረጃ ይሆናል? በፍጹም መሆን አይችልም! ማሳያዎችን እናንሳ ፡-
    - ክፋት ማየታችን አምላክ የለም የሚያስብል ከሆነ አምላክ ኖሮ ግን ደግሞ ክፋቶች እንዳሉ እንኳን የማያውቅ ቢሆንስ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል:: ሁሉን አዋቂ ያልሆነ አምላክ ቢሆንስ ያለው? (**አንባቢ ሆይ!** ይህ ጥያቄ ፍጹም አምላክ የለም ለሚሉ ለኤትስቶች እንጂ የአምላክን መኖር ለሚያምኑ የቀረበ አይደለም!)
    - ክፋት ማየታችን አምላክ የለም የሚያስብል ከሆነ አምላክ ኖሮ ክፋቶችን ማቆም ባይፈልግስ? ፍቅር የሆነ አምላክ ባይሆንስ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል! (**አንባቢ ሆይ!** ይህ ጥያቄ ፍጹም አምላክ የለም ለሚሉ ለኤትስቶች እንጂ የአምላክን መኖር ለሚያምኑ የቀረበ አይደለም!)

- ክፉት ማየታችን አምላክ የለም የሚያስብል ከሆነ የተለያ በሳይንስ ምርምር የማይደረስባቸው ተአምራቶች ለአምላክ መኖር ማስረጃ አይሆኑምን? በሕክምና አልድን ያለ በሽታ በጸሎትና በጸበል ሊድን መቻሉ ለአምላክ መኖር ማረጋገጫ መሆን አይችልምን?

**አግኖስቲስዝም** (Agnosticism) ፡- ይህ እሳቤ አምላክ ይኑር አይኑር አይታወቅም የሚል ነው፡፡ ተከታዮቹም አግኖስቲስት ይባላሉ፡፡ ይህም ሁለት ዓይነት እሳቤ ይኖረዋል ፡-

- ማንም ሰው የፈጣሪን መኖር አለመኖር በፍጹም ሊያውቅ አይችልም የሚል -
- ግላዊ በሆነ እሳቤ "እኔ ይኑር አይኑር አላውቅም ደግሞም አያስጨንቀኝም ሌላ ሰው ግን ምናልባት ሊያውቅ ይቻላል" የሚል -

**ሰው ባያምንም ሲቆጣጠረው የማይችል በራሱ ጥበብም ያልወቀው ከንድ ኃይል ከንዳለ ፍጥረት ሁሉ ይስማማል። ይህ የፍጥረት ሁሉ ጌታና ፈጣሪ መኖሩ የታወቀና የተረጋገጠባቸው ወይንም መኖሩን ከንድንቀበል የሚያስገድዱን ማስረጃዎች ከሉ ፡-**

### ሀ/ ሥነ-ፍጥረት

- አስተዋይ ሰው አእምሮውን ተጠቅሞ ሥነ-ፍጥረትን ብቻ ቢያስተውል የሚነግሩት ነገር አለ፡፡ ይህም ፍጥረት ሁሉ ከአንድ አካል ከፈጣሪ ጋር የማይቋረጥ ግንኙነት እንዳለው ማስተዋል የሚያስችል ነው፡፡
- በራሱ የተፈጠረና ለተፈጠረበትም የራሱ ዓላማ ብቻውን ሥልጣን ያለው ፍጥረት ማግኘት አይቻልም፡፡ ይህም አንድ ያልተፈጠረና የሁሉ ፈጣሪ የሆነ አምላክ እንዳለ ያስረግጥልናል፡፡
- በሳይንሱ እንደሚታመነው ሰውና አትክልት ወይም ዕፅዋት ምንም ስምምነት ሳይፈራረሙ የሰውን የተቃጠለ አየር ($CO_2$) አትክልት የአትክልትን ደግሞ ($O_2$) ሰው እንዴት መጠቀም ቻለ? ስንል ይህን ሁሉ በሥርዓት የዘረጋና በኪዳን ያጸና አንድ አምላክ መኖሩን እንድናምን እንገደዳለን፡፡

"ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል።" **መዝ 18፡1**

"የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ። ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፥"

**ሮሜ 1፡20-22**

- ሥነ ፍጥረት ለህልዎተ እግዚአብሔር አስረጂ ነው ማለት እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረት መኖር የኖረ ነው ማለት አይደለም፡፡
- በሸክላ ሠሪ መኖር ሸክላ ይኖራል እንጂ በተሰሩ ሸክላዎች ሸክላ ሠሪ እንደማትኖር ሁሉ ፍጥረት የተፈጠረው በእርሱ ህልዎት/መኖር ነው፡፡ ይሁን እንጂ እርሱም ራሱ ሥነ ፍጥረትን ለህልዎቱ/ለመኖሩ አስረጂነት ጭምር እንደፈጠረ በኋላ በቅዱሳት መጻሕፍት እንዲህ ተጠቅሷል፤

"ከዚህም ሁሉ ጋር መልካም ሥራ እየሠራ፥ ከሰማይ ዝናብን ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ሲሰጠን፥ ልባችንንም በመብልና በደስታ ሲሞላው ራሱን ያለ ምስክር አልተወም።" **ሐዋ 14፡17**

"አሁን ግን እንስሶችን ጠይቅ፥ ያስተምሩህማል፤ የሰማይንም ወፎች ጠይቅ፥ ይነግሩህማል። ወይም ለምድር ተናገር፥ እርስዋም ታስተምርሃለች፤ የባሕርም ዓሣዎች ይነግሩሃል። የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንዳደረገ ከእነዚህ ሁሉ የማያውቅ ማን ነው?" **ኢዮ 12፡7-10**

### ለ/ ሕገ ልቡና(የሕሊና ምስክርነት)

- ✓ ሰው አዋቂ እንደመሆኑ መጠን በሕሊናው የተቀረጸለት ሕግ አለ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ በዕለት ከተወለደ ሕጻን ጀምሮ ብንመለከት ዐይኑን በጣቱ አይጠነቁልም፤ ማንም ሰው መግደልን፣ መስረቅን.... የመሳሰሉት ምግባራት መጥፎ እንደሆኑ ያውቃል፤ ቢፈጽማቸውም እንደተሳሳተ ያውቃል፡፡
- ✓ ይህም የሕሊና መካሰስ እየፈጠረበት እንዲጨነቅ ያደርገዋል፡፡

"ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ።" **ሮሜ 2፡14-15**

### ሐ/ የሰው ልጅ የተፈጥሮ ዝንባሌ

- ሰው በተፈጥሮው ረዳት ፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች ቢኖሩኝ፣ ብሎ የተመኛቸውን ሁሉ ቢያገኝ ሌላ የሚመኘው አያጣም፡፡ ይህም ጎዶሎና ረዳት የሚያስፈልገው ጎዶሎውን የሚሞላለት ሌላ ረዳት ፈላጊ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
- ምንም እግዚአብሔርን ባያውቅና ባያምነው በኑሮው ግን ሁልጊዜ ይህን የማይደክም የማይሸነፍና የፈለጉትን ሊሰጥ የሚችል ረዳት ወይም አምላክ ይፈልጋል፡፡

### መ/ ቅዱስ መጽሐፍ

- ቅዱስ መጽሐፍ ሥራውን የሚጀምረው ፈጣሪን በፈጣሪነቱ እንዴት? መቼ? እና ለምን? እንደፈጠረ? በማስረዳት ነው፡፡

"በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።" **ዘፍ 1፡1**

- በማለት ይጀምራል እስከ ፍጻሜውም ይህንኑ ያስረዳል፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ ይልቁንም ፈጣሪ ራሱን ለሰው እንዴት እንደገለጸ የሚያስረዳ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ መመልከቱ የተሻለ ይሆናል፡፡

## <u>አስማተ እግዚአብሔር</u>

የአንድ አምላክን መኖር ለአመነ ሰው የአምላኩን ስም ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡ ሰው የአምላኩን ስም የሚያውቀው ጠርቶ እንዲያገኝበት ብቻ ሳይሆን ስመ ባሕርይውን የሚገልጥ ክብር ነውና የሚገባውን ክብር እንዲሰጥ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለባሕርዩና ግብሩ ተስማሚ የሆነ ስም ያለው አምላክ ነው፡፡ የአምላካችን ስም በራሱ የወጣና ራሱን ለሰው የገለጠበት እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል፡፡

- ☼ አባቶቻችን እንዳስተማሩን እግዚአብሔር "እግዚአብሔር " ነኝ ሲል የገለጠው ከሙሴ በኋላ ነው ከዚያ በፊት ግን "ሁሉን ቻይ አምላክ" (ኤልሻዳይ) ነኝ እያለ ይገልጥ ነበር፤ ከነአብርሃም በኋላ ሙሴንም በደብረ ሲና ያለው ይህንኑ ነው፡፡

**ዘጸ 3፡6** "እኔ የአባትህ አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ አለው። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ያይ ዘንድ ፈርቶአልና ፊቱን ሸፈነ።" በኋለም

**ዘጸ 6፡3** "ለአብርሃምም ለይስሐቅም ለያዕቆብም ሁሉን እንደሚችል አምላክ ተገለጥሁ፤ ነገር ግን ስሜ እግዚአብሔር አልታወቀላቸውም ነበር።"

- ☼ ይህም እግዚአብሔር ስሙን ለመግለጥ ጊዜ እንደሰጠ እኛም ስሙንና በስሙ የሚገለጠውን ክብሩን አውቀ ለመጥራት ማስተዋልና ጊዜ ሰጥቶ ማሰብ እንደሚገባን እንገነዘባለን፡፡
- ☼ ለሙሴ ከተሰጠው ዐሥር ሕግጋት መካከል የመጀመሪያው

**ዘጸ 20፡7** "የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና።የሚል ነበር፡፡"

- ☼ እስራኤልም በእነርሱ ቋንቋ እግዚአብሔር የሚለውን "ይሆዋ" ወይም "ያህዌ" እያሉ ይጠሩታል፡፡ ይሁን እንጂ ይህን ስም በዓመት ውስጥ አንድ ባሉት ታላላቅ በዓላት በሚደረግ ጸሎትና ምህላ ለዚያውም በሊቀ ካህናቱ ካልሆነ በቀር በግለሰቦች የግል ጸሎትም ሆነ የማኅበር ጸሎት አይነሳም ነበር፡፡
- ☼ በዚህ ፈንታ ግን ኤሎሄ/ኤሎሂም (አምላክ/አምላኬ)፣ አዶን/አዶኒ/አዶናይ (ጌታ/ጌታዬ)፣ ኤል/ኢለዮን/አሊዮን (ልዑል) በሚሉ አስማቶች(ስሞች) ይጠሩት ነበር፡፡
- ☼ እግዚአብሔር የሚለውን እንኳን ሲጠሩ ከላይ የተሰጠቀሱትንና ባሕርይውን የሚገልጡትን በመጨመር እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል፡፡ ለአብነትም፡-
- ☼ ጌታ እግዚአብሔር፣ ልዑል እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔር አምላክ፣ ሕያው እግዚአብሔር፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
- ☼ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ሰዎች ስመ አምላክን ለራሳቸው መጠሪያ በቀጥታ ተጠቅመውበት አልተገኙም፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ስም ከተደረገላቸው ውለታ ጋር አያይዘው እንደተጠቀሙበት ተመዝግቧል፡፡ ለአብነትም፡-
- ☼ ኢዮሳፍጥ (እግዚአብሔር ፈርዶአል)፣ ኢዮስያስ (እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አለ)፣ ኢዮራም (እግዚአብሔር አዳኝ ነው)፣ ኤርምያስ (እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ያደርጋል) የሚሉት ስሞች ከያህዌ ተዛርፈው የወጡ ሲሆኑ
- ☼ አዶንያስ (እግዚአብሔር ጌታዬ ነው)፣ አዶኒራም (ጌታዬ ከፍ ያለ ነው) የሚሉት ደግሞ "አዶናይ" የሚለውን ስመ አምላክ ተዛርፈው የወጡ ናቸው፡፡
- ☼ ኤልሳዕ (እግዚአብሔር ደኅንነቴ ነው)፣ ኤልሳቤጥ (እግዚአብሔር መሐላዬ ነው) የሚሉት ደግሞ "ኤል/አምላክ" ከሚለው የተዛረፉ ናቸው፡፡

## <u>ባሕርየ እግዚአብሔር</u>

- ○ የእግዚአብሔርን ባሕርይ የምንናገረው ከገለጠልን ውስጥ ጥቂቱን ነው፡፡ ይህም የሚሆንበት እኛ ሕሊና መሸከም የማይችለው ባሕርይ ስላለው ብቻ ሳይሆን ሰው መረዳት የቻለውን ያህል እንኳ የሚገልጽበት ቋንቋ ስለሌለው ነው፡፡
- ○ የሰው ልጅ እንኳን የእግዚአብሔርን ባሕርይ መርምሮና አሰላስሎ ሊረዳ እና እግዚአብሔር ያልገለጠለትን በራሱ መንገድ ሊያውቅ ይቅርና የራሱን ጸባይ እንኳን በቅጡ አያውቅም፤ ለዚህም ነው ብዙ ሰዎች ስለ ራሳቸው ማውራት የማይችሉት ማለትም ራሳቸው መግልጽና ስለ ማንነታቸው ማስረዳት የማይችሉት፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ሰው የውጭና ውስጥ የሰውነት ክፍሎቹኑ በዝርዝር አያውቃቸውም፡፡
- ○ ስለዚህ በዚህ ደካማ ሕሊና በዚህ ሕጹጽ ዕውቀት እንዴት ምሉዕ፣ ረቂቅ፣ ብርሃን፣ ማዕምረ ኵሉ/ሁሉን አዋቂ የሆነው ቅዱስ እግዚአብሔርን መርምሮ መረዳት ይቻላል? እንመረምረው ዘንድ ሕሊና እና አቅም የለንም!
- ○ ባሕርይው ስንልም የራሱ ገንዘብ ሆነ ከማንም ያልተቀበለው ማንም ማን ከእርሱ ሊወስድበት የሚቻለው የሌለ፤ ከዚህ ገንዘቡም ለፍጡር ሲሰጥ ከእርሱ የማይጎድልበት ከሌላው ጸጋን ሲነሳም ለእርሱ የማይጨመርለት ማለት ነው፡፡

ከዚህ በመቀጠል ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ እንመልከት፡-

### 📖 ቅዱስ ነው

- ቅዱስ ልዩ ማለት ሲሆን ለእግዚአብሔር ሲቀጸል ፍጹም ልዩ የሚል ትርጉም ይኖረዋል፡፡ እግዚአብሔር ፍጹም ልዩ የሚሆነው ከሕጸጽ/ከጉድለት ነጻ በመሆኑና ከክፋትና ከርኩሰት የተለየ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ሌሎቹንም የሚቀድሳቸው እርሱ ስለሆነ ነው፡፡ ለዚህም ነው "አቤቱ በቅድስና የከበረ እንደ አንተ ያለ ማን ነው?" ተብሎ የማይነጻጸር ቅድስናው የተመሰከረለት፡፡
- ይህ ቅድስና ለባሕርይው የሆነ ማንም ያልሰጠው ከማንም ያላገነው የራሱ ገንዘቡ የሆነ ነው፡፡ ይህ ማለትም የቅድስና ባለቤት እግዚአብሔር ነው ማለት ነው፡፡

መዝ 98፡5 "አምላካችን እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ አድርጉት ቅዱስ ነውና ወደ እግሩ መረገጫ ስገዱ"
"ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" ኢሳ 6፡3
"እኔ አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" ዘሌ 19፡2

### 📖 መንፈስ ነው

- እግዚአብሔር አካላዊ መንፈስ ነው፤

"ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው" መዝ 101፡25
"ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን" መዝ 131፡7

- የሚሉትና መሰል ጥቅሶች የእግዚአብሔርን አካላዊነት ያረጋግጡልናል፤ እርሱም ራሱ "ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር" ዘፍ 1፡26 በማለቱ አካልና መልክ ለው መሆኑን ገልጧል፡፡ ይሁን እንጂ እግዚአብሔርን በጠባቡ ሕሊናችን ባለው የቁስ አካል መልክና አካላዊ ቅርጽ ልንሰጠው አንችልም፡፡ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡
- ስለዚህም ለአካሉ ወሰን ለመልኩ ቅርጽ ልንሰጠው አንችልም፡፡

"እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ? ወይስ በምን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ?" ኢሳ 40፡18

- እርሱ ግን ለሰው እንደ አዕምሮው ስፋት እንደ ሃይማኖቱ ጽናት ሊሰወርበትም ለፈቀደው ደግሞ ራሱን ሊገልጥለት ይችላል፡፡
- በራሳቸው ጥበብ መንፈስነቱንም ሆነ አካላዊነቱን እናውቃለን ለሚሉ የሚሰወርባቸው መሆኑን

"መሰወሪያውን ጨለማ አደረገ፤ በዙሪያውም ድንኳኑ በደመናት ውስጥ የጨለማ ውኃ ነበረ፡፡" መዝ 17፡11

- ራሱን በራሱ ለሰው ባሕርይ በሚስማማ መንገድ እንዲህ ካልገለጠ በቀር እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ ማንም አላየውም ሊያየውም የሚቻለው ፍጥረት የለም፡፡ ፍጹም መንፈስ ነውና፡፡

"መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፡፡" ዮሐ 1፡18
"ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያየውም አይቻለውም፡፡" 2ኛ ጢሞ 6፡16 የሚሉት የማይመረመር መንፈስ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

- ስለምልዓቱና ስፋቱ (በሰማይና በምድር በአየርና በእመቅም የመላ ስለመሆኑ) ደግሞ "ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ ነህ ወደ ሲኦልም ብወርድ በዚያ አለህ፡፡ እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር በዚያ እጅህ ትመራኛለች ቀኝህም ትይዘኛለች፡፡" መዝ 138፡7-10

"መጠንና መመርመር የሌለበት እሳተ መለኮት በማኅጸንሽ አደረ፡፡ በምድራዊ እሳት እንመስለው ዘንድ አይገባም ለእሳትስ መጠን አለው፤ ልክም አለው፡፡ መለኮት ግን ይህን ያህላል፣ ይህንንም ይመስላል ሊባል አይችልም፡፡ ለመለኮት እንደ ፀሐይና ጨረቃ ክበብ፣ እንደ ሰውም መጠን ያለው አይደለም፤ ድንቅ ነው እንጂ፤ የሰው ሕሊና የመላእክትም አእምሮ በማይደርስበት በአርያም የሚኖር ነው እንጂ፡፡ ለመለኮት ወርድና ቁመት፣ ላይና ታች፣ ቀኝና ግራ ያለው አይደለም፣ በሁሉ የመላ ነው እንጂ፡፡ ለመለኮት የሚዘረጋበትና የሚሰበሰብበት ያለው አይደለም፤ ግዛቱ በሀገር ሁሉ ነው እንጂ፤ ለመለኮት በላይ ጠፈር በታችም መሠረት ያለው አይደለም፤ ጠፈሩ እርሱ መሠረቱም እርሱ ነው እንጂ፡፡ ለመለኮት ከምድር ከውስጥም የሆነውን ያነሳ ዘንድ መጎንበስ፣ ራስንም ዝቅ ማድረግ ያለበት አይደለም፤ ለጴጥሮስ እንዳሳየው ሁሉ በእጅ የተያዘ ነው እንጂ፡፡ ለመለኮት በሚታይ ገንዘብ በሚወስንም ገንዘብ ደረትና ፊት ኋላም ጀርባ ያለው አይደለም፤ በነደ እሳት የተሸፈነ ነው እንጂ፡፡ ነደ እሳት ግን እርሱ ነው፡፡ መለኮትስ ንጹሕና ጽሩይ ብሩህም ነው፡፡" ቅዳሴ ማርያም ቁጥር 47-53 (አባ ሕርያቆስ)

- ለር**ቀ**ቱም (ቀ ጠብቆ ይነበብ) ምሳሌ የለውም፡፡ ሊቃውንቱ ከመታሰብ በላይ መሆኑን ለማስረዳት ረቂቃን ፍጥረቱን በማነጻጸር ያስረዳሉ፡፡ ነፋስ ረቂቅ ነው፣ ከነፋስም የሰው ነፍስ ትረቃለች፣ ከሰው ነፍስም መላእክት ይረቃሉ፣ ከመላእክትም ርቀት ደግሞ ሕሊናቸው ትረቃለች፡፡ ይህችም የመላእክት ሕሊና ርቀት በቅድስት ሥላሴ ዘንድ እንደ አምባ እንደ ተራራ የገዘፈች ናት በማለት ያስረዳሉ፡፡
- በዚህ ር**ቀ**ት (ቀ ጠብቆ ይነበብ) እና ምልዓቱ እግዚአብሔር ሦስትነቱ በአንድነቱ ሳይጠቀለል፤ አንድነቱም በሦስትነቱ ሳይከፈል በአካላት መደባለቅና መቀላቀል ሳይኖር፤ በመለኮትም መለያየትና መከፋፈል ሳይኖር በር**ቀ**ት (ቀ ጠብቆ ይነበብ) እና በምልዓት የሚኖር የማይነገር አካላዊ መንፈስ ነው፡፡
- ይህንም እንደተሰጠን አቅም እንደተገለጠልን መጠን ለመናገር እንጂ ስለ እግዚአብሔር መንፈስነትና ሌሎችም ባሕርያቱ እንደ እግዚአብሔርነቱ እንናገር ከተባለ መናገር የሚቻለው **"የሚነገር አለመሆኑን"** ብቻ ነው፡፡

- ይሁን እንጂ እንደ አቅማችን እግዚአብሔርን መንፈስ ነው ስንል ሊዘነጉ የማይገባቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡ ምልዓቱ፣ ርቀቱ፣ የማይመረመር ስውር መሆኑ፣ ራሱን የሚገልጥ ከሱት(ግልጥ) መሆኑ፣ በአካላት መደባለቅ በመለኮት መለያየት የሌለበት መሆኑ ነው፡፡

📖 **ሁሉን ቻይ ነው**

- እግዚአብሔር በባሕርይው የሚሳነው የሌለ የወደደውን ሁሉ ያደርግ ዘንድ የሚቻለው አምለክ ነው፡፡ ፍቁረ እግዚአብሔር ኢዮብ

“ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንህ፣ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ” ኢዮ 42፡2

“በሰማይና በምድር በባሕርና በጥልቆች ሁሉ እግዚአብሔር የወደደውን ሁሉ አደረገ” መዝ 134፡6

- ቅድስተ ቅዱሳን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንበለ ዘር ጸንሰሽ ትወልጃለሽ ብሎ የነገራትን መልአኩን “እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ” ባለችው ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል “ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም” በማለት ከሃሌ ኵሉ መሆኑን ነግሮ አሳምኖአታል፡፡ ሉቃ 1፡37
- እግዚአብሔር በሙሴ በትር ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ እስራኤልን አሻግሮ ፈርዖንን አስጥሞአል፡፡ ወንዶቹ ዘር ከመተሩ ሴቶቹም ደም ከደረቁ በኋላ ሙቀት ልምላሜ ሰጥቶ አብርሃምና ሠራ፣ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ፣ ሐናና ኢያቄም ልጅ እንዲወልዱ አድርጓቸዋል፡፡
- በዘመነ ሥጋዌው ከሃሌ ኵሉነቱን(ሁሉን ቻይነቱን) “በሰው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል” ሉቃ 18፡27 በማለት አስረግጦልናል፡፡

📖 **ዘለዓለማዊ ነው**

- እግዚአብሔር የነበረ፣ ያለና የሚኖር አምላክ ነው፡፡ ይህም ማለት ጥንት የሌለው ጥንት፣ ዘመን የማይቆጠርለት መካከለኛ፣ ፍጻሜ(መጨረሻ) የሌለው ፍጻሜ ነው፡፡

“አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው፡፡ እነርሱ ይጠፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ፤ ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፤ እንደ መጎናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፤ ይለወጡማል አንተ ግን ያው አንተ ነህ፤ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም፡፡” መዝ 101/102፡ 27-28

  - በማለት ቅዱስ ዳዊት ለዘመኑ ሕልፈት ለባሕርይው ሞት እንደሌለበት ገልጧል፡፡
  - እግዚአብሔርን መወሰን አንችልምና ባሕርያቱ እነዚህ ብቻ ናቸው ብሎ ፍጡር ቆጥሮ ሰፍሮ መናገር አይቻለውም፡፡

ለማንኛውም ጥያቄና አስተያየት:- ☎ +251-9-10-67-98-99
ለቴሌግራም:- https://t.me/Jere_mi_ah
ሌላ አማራጭ:- siermiyas@gmail.com